የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፓ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ሚያዚያ 19 2015.

ቁጥር/REF NO: 8/256/556/15

ለሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት

<u>ባሉበት</u>

ጉዳዩ፡- <u>የ2015 ዕጩ ምሩቃን የሆኑና ለመውጫ ፈተና የሚቀመጡ ተማሪዎች መረጃን ይመለከታል፡፡</u>

ሚያዝያ 18 ክቡር የትምህርት ሚኒስትሩ በመሩት መድረክና የትምህርት ሚኒስቴርና የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ሥራ ሃላፊዎች በተገኙበት ከግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጋር የተያያዙ በርካታ ነጥቦች ላይ ውይይት ተደርጎ አቅጣጫዎች መቀመጣቸውና ውሳኔዎች መተላለፋቸው ይታወሳል፡፡ በእለቱ ውይይት ተደርጎ አመራር ከተሰጠባቸው ጉዳዮች አንዱ በ2015 ዓ.ም ማጠናቀቂያ የሚሰጠውን የከፍተኛ ትምህርት መውጫ ፈተና ይመለከታል፡፡

ስለሆነም በውሳኔው መሰረት፡-

1ኛ. ሁሉም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የ2015 እጩ ተመራቂዎችና የመውጫ ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎቻቸውን ሙሉ መረጃ ቀደም ብሎ በተላከው ቅፅ መሰረት እስከ ሚያዝያ 26 ቀን 2015 ዓ.ም. ለትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እንዲያስገቡ፣

2ኛ. የትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን የሚደርሰውን የእጩ ተመራቂዎች መረጃ በሥራ ላይ ካለው ህግና አሰራር አንፃር ህጋዊነቱንና ትክክለኛነቱን በማጣራት እስከ ግንቦት 4 ቀን 2015 ዓ.ም ለትምህርት ሚኒስቴር እንዲያስተላልፍ፣

3ኛ. የትምህርት ሚኒስቴር በባለሥልጣኑ ተረጋግጦ የሚደርሰውን የእጩ ተመራቂዎችና የመውጫ ፈተና ለመውሰድ የሚችሉትን ተማሪዎች ዝርዝር ከመጡበት ተቋማት ስም ጋር ይፋ የሚያደርግበት ቀን ግንቦት 7 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሆን ይህንንም ሥራ ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን እና ከግል ከ/ት/ቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ማህበር የተውጣጣ ቡድን እንዲፈፅመው ሆኖ፡-

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ትምህርት ሚኒስቴር

FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
MINISTRY OF EDUCATION

ስ: +251 11 155 3133
ፖ. ሳ.ቁ 1367፣ አራዳ ክፍለ-ከተማ,
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
T: +251 11 155 3133
P.O. BOX 1367, ARADA SUB-CITY,
ADDIS ABABA, ETHIOPIA
www.moe.gov.et
www.facebook.com/fdremoe
@fdremoe
info@moe.gov.et

ቀን/DATE: ____________________

ቁጥር/REF NO: ____________________

1. ዶ/ር ኢዮብ አየነው ከትምህርት ሚኒስቴር ......................... ሰብሳቢ
2. አቶ አዲስ ግዛው ከትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን ............. አባል
3. አቶ ሃብታሙ ገ/መድህን ከትምህርትና ሥልጠና ባለሥልጣን...... አባል
4. አቶ ተገኝ አለሜ ከግል ከ/ት/ቴ/ሙ/ት/ስ ተቋማት ማህበር ..........አባል

የተወከሉ መሆኑን እያስታወኩ ሥራውን በጥንቃቄና በኃላፊነት እንዲሰራ አሳስባለሁ፡፡

ከግል ተቋማት የሚመጣው የእጩ ተመራቂዎችና የመውጫ ፈተና የሚወስዱ ተማሪዎች መረጃ ከተቀመጠው ቀን ገደብና በህግ አግባብ ተቀብለው ማስተማር ከተፈቀደላቸው ተማሪዎች ውጭ ሆኖ ቢገኝ ለችግሩና ለሚወሰደው ቀጣይ እርምጃ ተቋማት ተጠያቂ መሆናቸውን ከወዲሁ እናስታውቃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ሳሙኤል ክፍሌ ኪዳኔ (ዶ/ር)
ሚኒስትር ዴኤታ

**<u>ግልባጭ</u>**

ለክቡር ሚኒስትር ጽ/ቤት

ለሚኒስትር ዴኤታ ጽ/ቤት (ከፍተኛ ትምህርት ልማት ዘርፍ)

ለአካዳሚክ ጉዳዮች መሪ ስራ አስፈጻሚ

**<u>ትምህርት ሚኒስቴር</u>**

ለትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን

**<u>አዲስ አበባ</u>**

ለዶ/ር ኢዮብ አየነው

ለአቶ አዲስ ግዛው

ለአቶ ሃብታሙ ገ/መድህን

ለአቶ ተገኝ አለሜ

**<u>አዲስ አበባ</u>**